# ይድረስ ለተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ በህዝብ ተወካዮች የፓርላማ አባል

የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ በ4ኛው አገራዊ ምርጫ ተወዳድረው አሸንፈው በአዲስ አበባ ህዝብ የአንደ ክፍለ ከተማ ህዝብ ወክለው በተወካዮች ምክር ቤት ፓርላማ ገብተው እየሰሩ ይገኛሉ።ይሁን እንጂ ዱባና ቅል ለየቅል እንደተባለ ሁኖ ህዝብ የሰጠዎትን ሓላፊነት ወደ ጎን በመተው በግል ጥቅም ታውረው የህዝብና የአገራዊ ጥቅም በመፃረር የከሰረ ፕሮፖጋንዳ በማስተጋባት ላይ ይገኛሉ።ድሮውም እንካን ዘንቦብሽ ------------- እንደሚባለው ከከሰረ የፖለቲካ ድርጅት አባል መልካም ነገር ይወጣል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል የርግብ ጫጩት እንደ መፈልፈል ይቆጠራል።

የተከበሩ ኣቶ ግርማ ሰይፉ በፓርላማ የገቡት በተቋቋመው ምርጫ ቦርድ እውቅና አግኝተው ነው።ይሁን እንጂ ምርጫ ቦርድን በመወንጀል ረገድ ቁጥር አንድ እርስዎ ነዎት።ፓርላማ የገቡትም ሁሉን የፓርላማ ውሳኔዎች አዋጀችና ደንቦችን በተቃውሞ ለመደምደም እንጂ በስነ አመክኖዮ ርትአዊ በሆነ rational and reasonable በሆነ አገባብ የፖለቲካ ልዩነት እንዳለ ሁኖ- በሚያስማሙ አገራዊ ጉዳዮች እየተስማሙ ከዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መርሆዎች በማገናዘብ ለአገራችንና ለህዝቦቿ የሚሰጠውን ፋይዳ ያለው አንደምታ በማገናዘብ ከግል የፖለቲካ ጥቅምና ፍጆታ ባሻገር ግራና ቀኝ ኣይተው ማሻሻያዎችን በማከል የመረጣቸውን የብዙሃን ድምፅ በማክበር ከመንግስት ጋር በሚያስማሙ እየተስማሙ በልዩነትም እንዲሁ ተቻችሎና ተደማምጦ አብሮና ተባብሮ መስራት ይገባዎት ነበር።ብልህነትና የፖለቲካ ብስለትም ያሳይ ነበር።

ከግል ዝናና የፖለቲካዊ ስልጣን ጥማት ይልቅ የህዝቡን ተጠቃሚኒት የህዝቡን የመቻቻል ባህልና ኣብሮነት የሚያጎላ ስራዎችን መስራት ከአንድ የፖለቲካ ድርጅትና ፖለቲከኛ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው።ነገር ግን በፖለቲካ ድርጅታቸው ዴሞክራሲ ያላሰፈኑ በፖለቲካ ድርጅታቸው በዴሞክራሲያዊ አመራር ዕጦረት የደረሰባቸውን ሽንፈት፣ ኪሳራና መፈረካከስ በመንግስት ላይ ዕርባና ቢስ ትችትና ወቀሳ እንዲሁም የማሳከክ አባዜ ተጠናውቶባቸው በአገር ውስጥና በውጭ የድረሱልኝ የጥሪ ደወል በማስተጋባት ላይ ይገኛሉ።ወጣወጣና እንደ ሸምባቆ ተንከባለለ------ማለት ይህ ነው።

የእነ አቶ ግርማ ሰይፉ በፖለቲካ ድርጅታቸው የደረሰውን የኢ- ዴሞክራሲያዊ አምባገነነ አመራርና በውጭ የሚኖሩ የከሰሩ ዲያስፖራዎች ጫንቃ የሚሽከረከር የአሻንጉሊት ድርጅት እንደ እምባይ ካብ ሲፈረካከስ ተቀራርቦና ተቻችሎ ቅራኔዎችን ከመፍታት ይልቅ በወጣት አባላት ላይ በመዝመት ስልጣን ያለ አግባብ በመጠቀም የፖለቲካ ድርጅቱ እንዳሆን አድርገውታል።

ስለዚህ በውስጡ ዴሞክራሲያዊ ባህል አሰራር ያላሰፈነ የፖለቲካ ድርጅት ለህዝብና ለአገር ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያጎናፅፋል ተብሎ ማመን አይቻልም ። ይልቁንም ባገኙት አጋጣሚ በፓርላማ ይሁን ባገር ውስጥ ለግል ሚድያዎችና ተቀማጭነታቸው ባገር ውስጥ ለሆኑት የውጭ ሚድያዎች የአገራችን በጎ ገፅታ ሳይሆን መጥፎውን፤ ዕድገታችን ሳይሆን ውድቀትን አንድነታችን ሳይሆን ልዩነታችን በማጉላት የፕሮፖጋንዳ ሲሳይ ሲሆኑ እናያለን።

**አስራጅ፤-** አቶ ግርማ ሰይፉ በአሜሪካ ሬድዮ ጣብያ የካቲት 2/6/2007 ዓ/ም ያደረጉት ቃለ-ምልልስ ስንመለከተው መሰረተ ልማት በተመለከተ'' በባቡር ትራንስፖርት ውድቀት እንዳጋጠመው ለፈለፉ' ይሁን እንጂ በፓርላማና በሌሎች መድረኮች እንደተገለፀው ፊዚካል ጥናትና ዲዛይን እንደተጠናቀቀና ቅድሚያ የተሰጠው ግን የአገራችና የአፍሪካ መዲና በሆነችው ውብ ከተማ በመዲናችን በአዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር መስመር መሆኑን የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በአንክሮ አበከረው የተናገሩት ነበር። ይህም ተግበራዊ ሆነ ፤ቀጣይ ምዕራፍ ምን እንደሚሆንም በዕቅድ የተያዘ መሆኑን እያወቁ ማንቋሸሽ የታከለበት መግለጫ ሰጡ።በተመሳሳይም የኤኮኖሚያችን ዕድገት በተመለከተ የዓለም ባንክ በቅርብ ቀን ባወጣው መግለጫ የድህነት ወለል ከነበረበት 55% ወደ 33% መውረዱን በግልፅ በማያወላዳ ቋንቋ በመግለፅ

ላይ እያለ የተከበሩ አቶ ግረማ ሰይፉ ግን ዓይኔን ግንባር ያድርገው በማለት ''እየተነገረን ያለው ቁጥር ስህተት ነው። 600 USD ይሉናል፤ 1000 USD ቢሉን ምን ታደርገዋለህ '' እየራበን ጠግባችሃል ይሉናል '' በማለት የዓይኔ ግንባር ያድርገው ቃለ-ምልልስ አደረጉ።

ይሁን እንጂ ቅድሚያ የሚሰጠው በአዲስ አበባ ያለው የትራንስፖርት ችግር መቅረፍ መሆኑን የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በግልፅ የተናገሩት በአሁኑ ወቅት እውን የሆነው ነው።ይህ በእርግጥ መመሰገን የሚገባው ቃል በተግባር የተረጋገጠበት መሆኑን ለማንም ኢትዮጲያዊ ገሃድ ነው ። ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው ሮይተርስ በመሰረተ ልማትና በኤኮኖሚ ዕድገት የአገራችን እንዲሁም የአፍሪካ በማገናዘብ በቅርብ ቀን ያወጣው ዘገባ መመልከቱ አንዱ ሌላ አስረጅ ነው ።

## (*Reuters) -Sun Feb 8, 2015 6:52am ES*

*At the heart of the state's "Growth and Transformation Plan" are railway, road and dam projects to give the landlocked nation cheap power and reliable transport, as well as the metro line - the first urban light railway network in Sub-Saharan Africa.*
*Hefty state-led investment has kept the economy of Africa's second most populous nation growing at more than 8 percent a year for over a decade,*
*Foreigners cannot invest in banking and telecoms and foreign retailers are barred, while Ethiopian banks are directed to buy low-yielding government development bonds.*
*"This is a country where, relative to rest of Africa, there is pretty good state capacity and a commitment to a development mission," said S. Kal Wajid, the outgoing Ethiopia mission chief for the International Monetary Fund.*
*But he said private business needed room to grow and generate income so the economy could reap greater benefit from the new projects. "Where you are making a lot of infrastructure investment, there is a risk that the pay-off may not be as big as you thought," he added.*
*Others in Africa have looked with envy at Asia's inexorable rise but few governments, if any, have proven as single-minded as Ethiopia has in mobilizing its resources in a bid to turn an agrarian nation of 96 million people into a manufacturing hub.*
*Yet it comes at a cost. The IMF said last year Ethiopia was "on the cusp" of shifting from low to moderate risk of debt distress. Total debt at about 50 percent of gross domestic product was still manageable, but tougher if it rises much more.*
*"In the next five-year plan, there should be a clear indication of a change of emphasis and a significant emphasis on the private sector," said Wajid, referring to the next Growth and Transformation Plan starting in July.*
የውጭ ሚድያዎች ሳይቀር የመሰከሩት ሃቅ በእነ አቶ ግርማ ሰይፉና ተከታዮቻቸው የሚያራግቡት የከሰረ ፕሮፖጋንዳ ዕርባና ቢስ መሆኑን የሚያጋልጥ ነው።ዳሩ ከጨለምተኛ ፖለቲከኝነት የሚመነጭ ነው።
እንደሚባለውም ሮምም በአንድ ቀን እንዳልተገነባች ሁሉ አሁንም ጥሩ ጅምር ነው። ይሁን እንጂ በግንባታው ይህ ይህ የመሰለ ችግር አለበት።መንግስት በዚህ ረገድ የአፈፃፀም ችግር አለበት ፤ገንቢ ሓሳቦችንና የሰላ ሂሶች መስጠት የነበረ የአዋቂ ፖለቲካኛ አቀራረብ ማሳያ ነው።ይሁን እንጂ ነገሩ ዱባና ቅል ለየቅል ተብሎ የለም/
የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ኤርትራን በተመለከተ ያሳዩት አቋም ሲገልፁ ''እኛ የሚያሳስበን ከኤርትራ ጋር ያለን አለመግባባት ሳይሆን በውስጣችን ያለው አለመረጋጋት ነው።የእኛ ጥያቄ ትኩረት አቅጣጫ በመቀየር እነሱ የፈለጉትን ለማድረግ እንዲችሉ ነው'' ሲሉ ተማጉተዋል ።በፓርላማ እንዲሁም ከአሜሪካ ሬድዮ ድምፅ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ገልፀዋል ።ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው እርስዎ እንኳን አዲስ ነገር አልተናገሩ።የሰለቸ ኩሸት ነው። ከዚህ በፊት በአገራችን ቀጥተኛነ ወቅታዊ አደጋ በተደቀነብን ወቅት The real and present danger ይኸውም በሶማልያ ፍርድ ቤቶች ህብረት በታወጀብን የጅሃድ ጦርነት ፤ አሸባሪው የኤርትራ መንግስት ተላላኪዎችን በማስረግ እኩይ ተግባር ሲፈፅም በውስጥ በሕጋዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሽፋን በማድረግ በውስጥ አርበኝነት በታመሰችበት ወቅት በወቅቱ በፓርላማ መቀመጫ በነበራቸው የተለያዩ የፓርቲዎች አመራር አካላት ኤርትራ በተመለከተ ከሰጡት መግለጫዎች ከወሰዱት አቋም የተለየ ነገር የለውም ።በዚሁ ወቅት የተከበሩ

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ፤ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፤ ዶ/ር መራራ ጉዲናና አቶ ቡልቻ መደቅሳ በፓርላማ የሰጡት መግለጫና የወሰዱት አቋምደግመውታል አቶ ግርማ ሰይፉ።

በዚሁ ወቅት አገራዊ ሃላፊነት የተሰማውና በአገራዊጉዳይ ከግል የፖለቲካፍጆታ ባሻገር አንድ የጋራ አገራዊ አስተሳሰብ በመፍጠርና የጋረ አቋም በመውሰድ አገራዊ ግዳጁን የተወጣው የኢትዮጲያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ኢዴፓ ብቻ ነበር። የሶማልያ ጀሃዲስት አሸባሪ በመ በህዝብና በመንግስት እንዱምኢዴፓ በወሰደው ፅኑ አገራዊ አቅም በአገራችን ላይ ተደቅኖ የነበረው አከርካሪው በመስበርና በመደምሰስ አሁን ላለንበት ብሩህ የተደላደለ ሰላምና የህዳሴ ጉዞ እውን እንዲሆን አስችለዋል። አገራዊና ህዝባዊ ሓላፊነት ለተሰማው ኢዴፓ አድናቆታችን እንገልፃለን።የብስል የፖለቲካ ድርጅት አርአያ መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ ህዝባችና መንግስታችን በኤርትራ ላይ ያለው አቋም ከዚህ በፊት ከነበረው የተለየ አቋም ኣይደለም።የኤርትራ መንግስት አሸባሪ መንግስት መሆኑን ከህግ ይልቅ ጉልበትን ፤ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፤ ከዕድገት ይልቅ ውድቀትን የሚያራምድ የሚናፍቅ ፤እንኳን ለሌሎች ህዝቦች አንድነትና ሰላም ሊመኝ ቀርቶ ለዜጎቹ የማይጨንቅ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከአሸባሪዎች ያለውን የጠበቀ ቁርኝት ፤ በሲና በርሃ ፤ በሊብያ በረሃና በሚድትራልያን ባህር ዜጎቹ ሲያልቁ ቅንጣት ታህል ሰብዊነት የማይሰማው መንግስት መሆኑንን የተገነዘበው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ሰ ሁለት ጊዜ ስ የጠጫለው ማዕቀብ ያልተነሳ መሆኑንየኤርትራመንግስት ከአሰባሪነት ባህሪው ያልተላቀቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው ።

ታድያ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ለዚሁ መንግስት ጥብቅና መቆማቸው ምን ሊባል ይቻል ይሆን።እርስዎ ከውጭ የሚኖሩ የጥፋት ኋይሎች ዲያስፖራ ከሚላክላቸው የአይዞህ ባይነት ዳርጎት ጋር የገቡት ቃል ኪዳን ላለማፍረስ ከሆነ ዙሮ ዝሮ ሃቁ መውጣቱ አይቀርም። ' ቦ ጊዜ ለኩሉ ' ነው ። በመረጠዎትን ህዝብ አንድ ቀን ተጠያቂ ይሆናሉ።

እንደሚታወቀውና ካለፈው ልምዳችን አንፃር ሲቃኝ በማነኛውምመለኪያ የኤርትራ መንግስት ለኢትዮጲያ ኢትዮጲያውያን አንዳችም የበጎ ምኞት የሌለው ይልቁንም ደካማ ኢትዮጲያ ተፈጥራ ሀብቷ በመመዝበር ለመክበር ካለው ጭፍን ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር የኤርትራ መንግስት ጉዳይ ከአቶ ግርማሰይፉ በላይ ተግባሩ ምኞቱ ምን እንደሆነ እናውቀዋለን።

የእነ አቶ ግርማ ሰይፉና ተከታዮቻቸው ሐቁ በውስጥ የድርጅት ሽኩቻ በተፈጠረው ውጥረት ፀረ ዴሞክራሲ አካሄድ የተተበተቡት አቶ ግርማ ሰይፉ ወጣቶችን በማግለል የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት ከድርጅት ከአባላት ጥቅም ይልቅ ለግል ጥቅማቸው ለማርከት ቅድሚያ በመስጠት በመንግስት ላይ ጣታቸውበመቀሰራቸው አግባብነት የለውም።በፓርላማ የገቡት በህዝብ ድምፅ አመካይነትብምርጫ ቦርድ እውቅና ኣግኝተው ነው። ታድያ ለህዝቡ ምን ሰሩ ቢባሉ መልስዎ ሁሉ ግዜ መንግስት የሚያቀርበውን ሪፖርት መቃወም፤መንግስት የሚሰራቸው የልማት ስራዎች ማንቋሸሽ ፤ እየተመዘገቡ ያሉት የኤኮኖሚ ዕድገት ማጣጣልና ሽሙጥ መጋለብ ነው የሚል እንደሚሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

በመጨረሻ የተከበሩ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ቦርድን ከአንድ የህዝብ ተወካይ እንዲህ ዓይነት ማጣጣል ምን ይባላል/ ነው ወይስ ከኔ በኋላ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው እንስሳ ዳግም እንደማይወዳደሩና እንደማይመረጡ ስላወቁ ነው።ይህም ብቻ አይደለም የከሰረ ፖለቲከኛና የፖለቲካ ድርጅት ከዚሁ የዘለለ የተሻለ ነገር ይጠበቃል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል የርግብ ጫጩት እንደመፈልፈል ይጠበቃል።
ስለዚህ ህዝብ ና መንግስት ሰላማችን ልማታችንነ ዕድገታችን አገራዊ ምርጫችን በተሰካ ሁናቴ ለማስቀጠል ያላንዳች የፀጥታ መሰናክል አብረን ተባብረን መስራት ይጠብቅብናል።

*ገ/ፃድቃን ከበደ*
*የካቲት 4/6/2007*